# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!

**ስለ አራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ሰምተሃል?**

፩. እግዚአብሔር ስለሚያፈቅርህ ለሕወትህ አስደናቂ እቅድ ሰጥቶሃል?

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሐንስ 3፡16

፪. ሰው ኃጢአተኛ የሆነ ባህርይ ስላለውና በዚህም ምክንያት ከእግዚአብሔር ስለ ተለየ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅርና እቅድ ሊለማመድ አይችልም።

"ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ሮሜ 3፡23

፫. ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ በመሞቱ በእርሱ በኩል ብቻ ሰው ወደ እግዚአብሔር ይደርሳል።

"እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።" ዮሐንስ 14፡6

፬. ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አዳኛችንና ጌታችን አድርገን በመቀበል እግዚአብሔር አምላክ ለኛ ያለውን ፍቅርና እቅድ ልናውቅና ልንለማመድ እንችላለን።

"ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው።" ዮሐንስ 1፡12

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በምጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

**ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-**
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m.
አርብ 7፡00 p.m. -- 9፡00 p.m.

የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን

Chicago Yemsrach Evangelical Church

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10




"በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ።"
(ዮሐ. 7:38)

| | |
|---|---|
| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1፡30 p.m. -- 4፡30 p.m. |
| **July 14, 2019** | **ሐምሌ 7፤ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

| | |
|---|---|
| ጸሎት ................. | እሕት (እትዮ) ሰላም ምትኩ |
| አምልኮ...................... | የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን |
| ፕሮግራም መሪ .......... | ወንድም ጸደቀ ጴጥሮስ |
| ቃል ............. | ወንድም ሲሳይ መሸሻ |
| ማጠቃለያ ................. | ፕሮግራም መሪ |

### የሳምንቱ ጥቅስ

“እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።”

(ዮሐ. 4፡14)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች**

| መሪ | ቀን | አድራሻ |
|---|---|---|
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### የሕይወት ውኃ

ጌታ በምድር በነበረበት ጊዜ አይሁድ ከሳምራዊያን ጋር ስለማይተባበርሩ ምንም እንኳ ከይሁዳ ወደ ገሊላ ለመሄድ አቋራጭ የነነበረው መንገድ በሰማሪያ በኩል ቢሆንም አይሁዳዊያን ግን አቋራጩን መንገድ አይመርጡም ነበር። በዮሐንስ 4 ላይ እንደምንመለከተው ግን ጌታ ኢየሱስ በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆኖበት ነበር። ምን ግድ አለው ብለን ብንጠይቅ ግድ ያለው ነገር ቢኖር መደረስ ያለባት ነፍስ ነበረች። ከክፍሉ እንደምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ መንገድ ከመሄድ ደክም በሰማሪያ፣ ሲካር ከተማ በያቆብ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። ጊዜው ቀትር ላይ ነበር። በዚያኑ ሰአት ደግም ከሰማሪያ አንዲት ሴት ውሃ ልትቀዳ መጣች።

ይህቺ ሴት የተቸገረች ሴት ነች። በመጀመሪያ በምንም መልኩ በቀጥር ውሃ ለመቅዳት ወደ ጉድጓድ አይመጣም። ውሃ የሚቀዳው ወይ በጠዋት ነው አለያው ጥላ ሲበርድ ነው። በልማድ ቀትር ጋኔን የሚወጣበት ነው። ለዚህም ሳሆን አይቀርም ቃሉ እግዚአብሔር ከቀትር ጋኔን እንደሚጠብቀን የሚናገረው። (መዝ. 91፡6) ስለዚህም በቀትር ሰው ወደ ውሃ ጉድጓድ ዝር አይልም። ይህች ሴት ግን ውሃን በቀትር ትቀዳለች። ተሰውራ-- ሰው ሳያያት የምትወጣና ይምትገባ ትመስላለች። ስለዚህም ከማህበረሰብ የተገለለች ሴት እንደነበረች የክፍሉ አውድ ያሳያል። ይህቺ ሴት የተጠማች ሴት ነች። የተጠማችው ውሃ ሳይሆን ሕይወት የተጠማች ሴት ነበረች። ብዙ ባሎች በመቀያየር ጥማቷን ለማርካት ሞክራለች። አምስት ባሎች አግብታ የፈታች አሁን ባሏ ካልሆነ ስድስተኛ ወንድ ጋር የምትኖር ናት። የባሎች መቀያየር የነፍሷን ረሃብ አላጠገበም። ሴቲቱ በሳምራዊነቷም በሴትነቷም በይሁድ የተናቀችም ነበረች። ሴቲቱ የእምነትም ችግር ነበራት። ለእግዚአብሔር የት ወይንም እንዴት እንደሚሰገድ አታውቅም።

እንግዲህ ግታን በሰማሪያ እንዲያልፍ ግድ ያለው የዚህች ቆስቋላ ሴት የሕይወት ጥም ነበር። የውስጥ ጥማቷን የሚያውቅ ጌታ “ተጠማሁ” ብሎ ቀረባት። ሰው ቀርቧት የማይውቅ ይህች ሴት አይሁዳዊ ውሃ አጠጪኝ ቢላት ተገረመች። እንዴት ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከኔ ውሃ ትለምናለህ አለችው። በውስጣ ግን “ጉዴን ባያውቅ” ነው ማለቷም አይቀርም። ጌታ ግን እርሱን ብታውቅ ጥማትዋን ሁሉ የሚፈውስ የሕይወትን ውሃ እንደሚሰጣት ተናገራት። እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ለዘላለም አይጠማም አላት። ይልቁንም ከጌታ ውሃ የሚጠጣ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል አላት።

ወገኖቼ:- ለነፍሳችን እርካታ የሚሰጠው ጌታ ብቻ ነው። ብዙ የውሃ አይነት ጠጥተን ለመርካት ሞክረን ይሆናል። በገንዘብ ውሃ ነብስ አትረካም፤ በእውቀት ውሃ ነፍስ አትጠግብም፤ በዝና ውሃ ጥሙ የተቆረጠ የለም፤ የስልጣንም ውሃ ነፍስን አያሳርፍም። ጌታችን ለዚች ለተጠማችና ለተቸገረች ነፍስ እንዳላት “ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል” (ቁ.13)። ነፍስን የሚያረካም ነፍሳችን ፈጣሪዋንና ጌታዋን ስትገናኝ የምትጠጣው የሕይወት ውኃ ብቻ ነው። ያንጊዜ ጥማትን የሚቆርጥ ምንጭ ከውስጥ ይፈልቃል። ምንጩ በምፈልቅበት ጥማት የለም። ይህቺም ሴት የውስጧ ጥም ሲቆረጥ እንስራዋን ጥላ ይህንን የሕይወት ምንጭ ለሌሎች ለመናገር ሮጠች። ወገኖቼ:- በውስጣችን የሕይወት ምንጭ አለ። ያሳረፈንና የሚያሳርፈን ይሄ የሕይወት ምንጭ ብቻ ነው። ክብር ለዘላለም ለጌታ ይሁን!